# ብሄራዊ የሀዘን ቀኑ ዛሬ ተጀምሯል



በጋምቤላ ክልል በታጣቂዎች ህይወታቸው ያለፉ ንፁሃን ዜጎችን ለማሰብ የሁለት ቀናት ብሄራዊ የሀዘን ቀን ተጀመረ።
የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህይወታቸው ያለፉ ንፁሃን ዜጎችን ለማሰብ ትናንት የሁለት ቀናት ብሄራዊ የሀዘን ቀን ማወጁ ይታወሳል።

ዛሬ እና ነገ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በውጭ በሚገኙ የኢትዮጵያ ኢምባሲዎችና ቆንስላ ፅህፈት ቤቶች ለሁለት ቀናት የሀገሪቱ ሰንደቅ አላማ ዝቅ ብሎ ይውለበለባል።

በተመሳሳይ ንብረትነታቸው የኢትዮጵያ የሆኑ መርከቦችም ከዛሬ ጀምሮ የኢፌዴሪ ባንዲራ ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ የሚያደርጉ ይሆናል።

ምክር ቤቱ መንግስት በታጣቂዎቹ ታፍነው የተወሰዱትን ህጻናት ለማስለቀቅ እና ታጣቂዎች ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስቧል።

እንዲህ አይነት ጥቃቶች በተለያየ ጊዜያት መልኩን ቀያይሮ የሚከሰት መሆኑን የጠቆመው ምክር ቤቱ፥ እንዲህ አይነት ጥቃቶችን በዘላቂነት

ለመካላከል እና ለማስቆም በሚቻልበት ዙሪያ ላይ መሰራት እንዳለበትም አስታውቋል።

ባሳለፍነው አርብ ምሽት በጋምቤላ ክልል ኑዌር ዞን በሚገኙ ሶስት ወረዳዎች በደቡብ ሱዳን በኩል ድንበር ሰብሮ በመግባት በንጹሃን ዜጎች ላይ በፈጸሙት ጥቃት ቁጥራቸው 182 ሰዎች መገደላቸው ይታወሳል።

እንዲሁም ቁጥራቸው 108 የሚደርስ ህጻናት በታጠቁት ሀይሎች ታፍነው ተወስደዋል።

የኢፌድሪ መከላከያ ሰራዊትም ጥቃት ፈጻሚ ወንበዴዎችን ድንበር በመሻገር እርምጃ እየወሰደባቸው ሲሆን፥ ከ60 የሚበልጡ ጥቃት ፈጻሚዎች ተገድለው የጦር መሳሪያም ተይዟል።

በአሁኑ ጊዜም በታጣቂዎች ታፍነው የተያዙትን የማስለቀቁ ዘመቻ ተጠናክሮ ቀጥሏል።